www.chilot.me

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ሰባተኛ ዓመት ቁጥር ፮
አዲስ አበባ ህዳር ፳፫ ቀን ፪ሺ፲፫ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

27th Year No.6
ADDIS ABABA December 2nd, 2020

**<u>ማውጫ</u>**

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፳፱ /፪ሺ፲፫ ዓ.ም

የኤክሳይዝ ታክስ (ማሻሻያ) አዋጅ………ገጽ ፲፪ሺ፱፻፲፪

ማረሚያ ቁጥር ፲፩/፪ሺ፲፫…………………ገጽ ፲፪ሺ፱፻፲፫

**<u>CONTENT</u>**

Proclamation No.1229/2020

Excise Tax (Amendment) Proclamation ……Page 12912

Corrigendum 11/2013…………………………Page 12913

**አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፳፱/፪ሺ፲፫**

**<u>የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ</u>**

ኮቪዲ ፲፱ ባስከተለው ተፅዕኖ ምክንያት የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች በማምረት ወይም አገልግሎት በመስጠት ሥራ ላይ የተሠማሩ ፈቃድ ሳይኖራቸው ሥራቸውን ሊያከናውኑ የሚችሉበትን የጊዜ ገደብ ማራዘም አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀፅ ፶፭(፩) እና (፲፩) መሰረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

**፩.<u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ አዋጅ “የኤክሳይዝ ታክስ (ማሻሻያ) አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፳፱ /፪ሺ፲፫” ተብሎ ሊጠቀስ ይቻላል፡፡

**፪.<u>ማሻሻያ</u>**

የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፹፮/፪ሺ፲፪ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፦

የአዋጁ አንቀጽ ፵፫ (፩) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፵፫ (፩) ተተክቷል፦

**PROCLAMATION NO.1229 /2020**

**<u>A PROCLAMATION TO AMEND THE EXCISE TAX PROCLAMATION</u>**

**WHEREAS,** due to COVID-19 pandemic crisis, it has become necessary to extend the period in which persons engaged in the manufacture of excisable goods or provisions of services may continue to do so without having the license;

**NOW, THERFORE**, in accordance with Article 55 sub-articles (1) and (11) of the Constitution Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

**1.<u>Short Title</u>**

This Proclamation may be cited as “Excise Tax (Amendment) Proclamation No. 1229/2020”.

**2.<u>Amendment</u>**

The Excise Tax Proclamation No.1186/2020 is hereby amended as follows:

Article 43(1) of the Proclamation is deleted and replaced by the following new Article 43(1).

www.chilot.me



“፵፫(፩).በዚህ አዋጅ ምዕራፍ ፫ ክፍል ፩ ፈቃድ ስለማውጣት የተደነገገው ቢኖርም የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች በማምረት ወይም አገልግሎት በመስጠት የተሠማራ ማናቸውም ሰው ፈቃድ ባይኖረውም ወይም ባይመዘገብም እስከ የካቲት ፴ ቀን ፪ሺ.፲፫ ዓ.ም ድረስ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች ማምረት ወይም ወደ አገር የማስገባት ወይም አገልግሎት የመስጠት ሥራ ማከናወን ይችላል፡፡”

“43.1. Notwithstanding provisions of Chapter 3 Part 1 of this Proclamation which provides for licensing, persons engaged in the manufacture of excisable goods or provisions of services may continue to do so until March 9th, 2021 without having the license Registration.”

## ፫.አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ከፀደቀበት ህዳር ፫ ቀን ፪ሺ.፲፫ ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

## 3. Effective Date

This Proclamation shall enter into force on the date of its ratification on November 12th Day of 2020 by the House of People’s Representatives.

**አዲስ አበባ ህዳር ፳፫ ቀን ፪ሺ.፲፫ ዓ.ም**

**ሳህለወርቅ ዘውዴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ**

**ሪፐብሊክ ፕሬዝዳንት**

**Done at Addis Ababa On the December 2nd Day of , 2020.**

**SAHILEWORK ZEWDE**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

## ማረሚያ ቁጥር ፲፩/፪ሺ.፲፫

**በአዋጅ ቁጥር ፩ሺ.፩፻፸፰/፪ሺ.፲፪ በሰው መነገድ እና ሰውን በህገወጥ መንገድ ድንበር የማሻገር ወንጀልን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ አንቀጽ ፫(፪) እንደሚከተለው ይነበብ**

"፫(፪) ማንኛውም ሰው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ለተመለከቱት የብዝበዛ ዓላማ በኢትዮጵያ ግዛትም ውስጥም ሆነ ከኢትዮጵያ ግዛት ውጪ መዳረሻ ቦታ ለማድረስ በዛቻ ፣በኃይል፣ በማገት፣ በመጥለፍ፣ ወይም ሌላ የማስገደጃ ዘዴ በመጠቀም፣ በማታለል ፣ የተስፋ ቃል በመስጠት፣ ሥልጣንን አላግባብ በመጠቀም ፣የሰውን ተጋላጭነት በመጠቀም ወይም ስለሌላው ኃላፊነት ያለበትን ሰው ፈቃድ ለማግኘት መደለያ ወይም ጥቅም በመስጠት ወይም በመቀበል ሌላውን ሰው የመለመለ ያጓጓዘ፣ወደ ሌላ ያስተላለፈ ፣ያስጠለለ፣የደበቀ ወይም የተቀበለ እንደሆነ ከሰባት ዓመት እስከ አስራ ሁለት ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራትና ከአርባ ሺ.ህ እስከ አንድ መቶ ሺ.ህ ብር በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል"፡፡

## Corrigendum 11/2013

**Prevention and Suppression of Trafficking in Persons and Smuggling of Persons Proclamation on 1178/2020 Article 3(2) read as follows.**

"3(2) Any person who recruit, transport, transfer, harbor, hide or receipt another person, to deliver at place of destination within or outside territory Ethiopia, by means of threat or use of force or other means of coercion, or of abduction, of fraud, of deception, of abuse of Power or of a position of vulnerability, or by the giving or receiving of payments or benefits to achieve the consent of a person having control over the person, for the purpose of exploitation provided under sub-article (1) of this article shall be punishable with rigorous imprisonment from seven years to twelve years and with fine from twenty thousand to one hundred thousand Birr," .

;

www.chilot.me